# “በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም”

**ያዕቆብ በኃይሉ**

**(ክፍል ሁለት)**

❖ **አቆጣጠሮቹ በሙሉ እ.ኤ.አ ናቸው**

በክፍል አንድ ፅሑፌ ላይ የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር በምስራቅ አፍሪካ ላይ ያካሄደውን የሽብር ስትራቴጂ በመጠኑም ቢሆን ለማመላከት ሞክሬያለሁ። በዚህኛው ክፍል ደግሞ፤ ይህ በመንግስትነት ተደራጅቶ የማፍያ ስራን የሚከውን ቡድንን በአጣሪ ቡድኑ ዓይን እንዲህ እንመለከተዋለን።...

...እንደ ኦብነግ ሁሉ ኦነግም ከኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት ጊዜ ጀምሮ ከኤርትራ ዕርዳታ በማግኘት ላይ ያለ ታጣቂ ሃይል ነው፡፡ ኤርትራ ከኦነግ ጋር በሶማሊያ ምድር የምታደርገው እንቅስቃሴ ቀደም ባሉት የአጣሪ ቡድኑ ዘገባዎች ተጠናቅሯል። ኦነግ በአስመራ ጽሕፈት ቤት ከፍቶ መንቀሳቀስ ከጀመረ ከአስር ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ሲሆን፤ ኤርትራን ምቹ የስልጠና እና የዘመቻ ማዘዣ ማዕከል አድርጎ ይጠቀምባታል፡፡ ታዲያ አብዛኛዎቹን እነዚህን መረጃዎች ከቀድሞ የኦነግ አባላት ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፤ በዚህኛው የአጣሪ ቡድኑ የሥራ ዘመንም ዳግም ተመስክረዋል፡፡

ኦብነግ በኤርትራ መንግስት ላኪነት 16ኛውን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤን ለማደናቀፍ ሞክሯል። እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ደህንነትና ፌዴራል ፖሊሲ ከጥር 31 እስከ 32 ቀን 2011 አዲስ አበባ ሊካሄድ ታቅዶ የነበረውን 16ኛውን የአፍሪካ ህብረት ልዩ ስብሰባ ለማደናቀፍ በአዲስ አበባና በዙሪያዋ የታቀዱ የፈንጅ ጥቃት ዒላማዎችን አከሸፈዋል። ምንም እንኳን ዘመቻውን በተግባር ለመተርጎም የተንቀሳቀሰው ኦነግ ቢሆንም፤ ሴራው የተጸነሰው፣ የተቀነባበረው፣ የተደገፈውና የተሰማራው በኤርትራ መንግስት የውጭ ዘመቻዎች ዳይሬክቶሬት አማካኝነት በጄኔራል ጠዓመ ጎይትኦም አመራርነት ሰጪነት ነው፡፡ ሴራው እንደታቀደው ተተግብሮ ቢሆን ኖሮ፤ የበርካታ ንፁሃን

ዜጎችን ህይወት በመቅጠፍ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከማውደሙም በላይ፣ የአፍሪካ ህብረት ስብሰባንም ያደናቅፍ ነበር፡፡ የዘመቻው ጥንስስ እንዲህ ነበር።…

ዘመቻው የታቀደው የኤርትራ ብሔራዊ ደህንነት ኤጀንሲ የመጀመሪያዎቹን የኦነግ ታጋዮች በ2008 መልምሎ ስልጠና መስጠት በጀመረበት ወቅት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ጦር በደረሰበት ከፍተኛ ኪሳራ ተንኮታኩቶ ከተበታተነ የኦነግ ታጣቂዎች የተረፈው ፈቃዱ አብዲሳ ጉሱ የተባለ ግለሰብ አንድ በኬንያ የሚኖር የኦነግ አባል ወዳጁ በ2008 ራሱን “ገመቹ አያና” እያለ ከሚጠራ ኤርትራዊ ኮሎኔል ጋር አገናኘው፡፡ ከዚያም ገመቹ (ቆርቾ) ከሶስት የኦነግ አባላት ጋር በሱዳን በኩል አድርጎ ወደ ኤርትራ እንዲጓዝ ትዕዛዝ ሰጠው፡፡

ፈቃዱ ኤርትራ እንደ ደረሰም በገመቹ እየታገዘ የፈንጅ ንድፈ -ሃሳብን ለሳምንታት ካጠና በኋላ፣ በአስመራና አካባቢዋ እየተዘዋወረ በተግባር የተደገፈ ትምህርት ቀሰመ፡፡ በተማሪዎቹ ዘንድ “ወዲ እያሱ” እየተባለ የሚሞካሸው ዋና አሰልጣኙ ኤርትራዊው መኮንን ነው፡፡ ፍቃዱ ስልጠናውን እንዳጠናቀቀም አዲስ አበባ ተጉዞ ራሱን ከከተማይቱ ጋር እንዲያለማምድ ትዕዛዝ መቀበሉን ለአጣሪ ቡድኑ ተናግሯል፡፡

ከሁለት ወራት በኋላ ደግሞ ፈቃዱ ወደ ኤርትራ በመመለስ ልዩ ልዩ ወታደራዊ ክህሎቶችን መጀመሪያ ደቀ መሃሪ ከዚያም ኢን ካምፕ ውስጥ አጠና፡፡ ኢን የ2009 ቀሪ ወራቶችን ከሌሎች የኦነግ ሰልጣኞች ጋር ያሳለፉበት የስልጠና ማዕከል ነች፡፡ በዚያን ወቅት “ደምሒት” የሚባል የትግራይ ሚሊሻ ቡድን በኢን ስልጠና ይወስድ እንደነበር ፈቃዱ ተናግሯል፡፡ ስልጠናውን በኢን እየተከታተለ በነበረበት ወቅት፣ የኤርትራ የደህንነት ሰዎች በኮሎኔል ገመቹ አማካኝነት ኦማር እድሪስ ሞሃመድ የሚባልና በኋላም የአዲስ አበባውን ዘመቻ የመራውንና ጂቡቲ የሚኖረውን የኦነግ ካድሬ መልምለዋል፡፡ ኦማር ከአጣሪ ቡድኑ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ፣ ኦነግን የተቀላቀለው በ2003 ሙልባራ (ጋሻ ባርካ) እንደሆነና “ሓዲስ ማእስከር” የሚባል ስፍራ ስልጠና ከወሰደ በኋላ፣ ቀስ በቀስ ከፍተኛ ኃላፊነት እንደተቆናጠጠ ይገልጻል፡፡

በወርሃ-ረመዳን (ነሃሴ/መስከረም 2009) ከኦነጉ ሊቀመንበሩ ዳውድ ኢብሳ ጋር እንደተገናኘና ከአንድ ኤርትራዊ መኮንን ምስጢራዊ ተልዕኮ ስለሚሰጠው የስልክ ጥሪ እስከሚደርሰው ድረስ በትዕግስት እንዲጠባበቅ ተነግሮታል፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ አምስት አዳዲስ ምልምሎችን ወደ ኤርትራ እንዲያመጣ ትዕዛዝ ከሰጠው ኮሎኔል ገመቹ ጋርም

ተገናኙ፡፡ እናም የዳዳ’ዓቱን ድንበር በማቋረጥ ጅቡቲ ደረሰ፡፡ ከአምስቱ አንደኛው የነበረው ኢማም ሰዒድ አህመድ እንዳረጋገጠው፤ ቡድኑ ከፍቃዱ ጋር እንዲሰለጥን ተመድቦ ወደ ኢን ተልኳል፡፡

ኡመር ደግሞ (በመጋቢት 2010) ወደ ኤርትራ ተጠርቶ ከገመቹና ጠዓመ ጋር በአስመራ ሆቴል መከረ፡፡ ጠዓመ ለኡመር ለከተማ ዘመቻ የሚያገለግል የፈንጅ ስልጠና እንደሚወስድ ካስረዳው በኋላ፤ ከጅቡቲ ካመጣቸው አምስት ምልምሎች ለመሰል ዓላማ የሚሆኑ ሁለት ሰዎችን መርጦ እንዲያመጣ አዘዘው፡፡ ከዚያም ኡመር በሃሰት ስም “ያሃ” እያሉ ከሚጠሩት ምልምል ሰልጣኞች ምረቃ በዓል ላይ በመገኘት ጠዓመ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት አብዱል ቃድርን “ጉርቴ” እና በቅፅል ስሙ “ድሮግባ” እየተባለ የሚጠራውን ሰኢድ መሐመድ የሱፍን መረጠ፡፡

ከዚያም የሁለት ሳምንት በንድፈ- ሃሳብና በተግባር የተደገፈ ስልጠና በአስመራና አካባቢዋ ከወሰዱ በኋላ፤ ከጅቡቲ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ ዲፖ ውስጥ ያሉ የኢትዮጵያ ቦቴ ተሽከርካሪዎችን ለማጋዬት የሚያስችለውን ዝግጅት እንዲያደጉ በሚያዚያ መገባደጃና በግንቦት መግቢያ 2011 ላይ ለሶስቱም ግዳጅ ተላለፈላቸው፡፡ ዕቅዱ ከመተግበሩ በፊት ጠዓመ ኡመርን ላልታወቀ ጉዳይ ወደ ኤርትራ ተመልሶ እንዲመጣ ደወለለት፡፡

ኡመርና ሁለት ጓደኞቹም ጅቡቲ ለሳምንታት ያህል ወታደራዊ ቅኝት ካደረጉ በኋላ፤ በእግራቸው ወደ ኤርትራ አቀኑ፡፡ እሱና ሌሎች 10 የኦነግ ታጣቂዎች የእግረኛ ስልጠና እየወሰዱ ዕውቀታቸውን እንዲያሻሽሉ ደግሞ ወደ ኢን ተላኩ፡፡ የዚህ ስልጠና አስተባባሪ ኮሎኔል ጀማል ሲሆን፤ የቡድኑ መሪ ደግሞ ኡመር ነበር፡፡ ሥልጠናው እንደተጠናቀቀም፤ ጠዓመ ኡመርን አስጠርቶ አዲሱ የጥቃት ዒላማቸው አዲስ አበባ መሆኗን አስረዳው፡፡

መጋቢት 2010 የስምሪት ቃጭሉ ከመሬሁ ቀደም ብሎ ፈቃዱና ሌሎች ሰልጣኞች ወደ አስመራ ተልከው በተንቀሳቃሽ ስልክ ፍንዳታን የማቀነባበር ጥበብንና የመካኒካል ሰዓት ቁጥጥርን አስመልክቶ በወዲ እያሱ አማካኝነት አጭር ስልጠና ተሰጣቸው፡፡ የፈቃዱ ቡድን አባል የሆነው ሰይፈ ጫላ በዳዳ እንደሚለው፤ እሱና ሌሎች ስለ ፈንጅ ዕውቀት የሌላቸው አባላት ፈቃዱ የወሰደውን ዓይነት መሰረታዊ ስልጠና ከተሰጣቸው በኋላ፣ በጠዓመ አማካኝነት ዳግም ስለ ዘመቻ ስለላና ስለመልሶ ማጥቃት መመሪያ ወስደዋል።

ከዚያም ፈቃዱ ከአባላቱ ጋር ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ እንዲሁም ፈንጂዎችንና መሰል ተጨማሪ አቅጣጫዎች እስኪሰጧቸው ድረስ እንዲጠባበቁ ትዕዛዝ አስተላለፉለት፡፡ ፈቃዱ አዲስ አበባ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ከገመቹ ጋር ቢያንስ 27 ጊዜ በስልክ ውይይት እንዳደረገ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በየጊዜው ከባህር ማዶ የሚላከው ገንዘብ ይጭነቀው እንጂ፣ ፈቃዱና የቡድን አባላቱ የአዲስ አበባ ኑሮ አልከበዳቸውም፡፡ ሲፈን ጫላ በዳዳ ለአጣሪ ቡድኑ እንደተናገረው፣ ገመቹ ኬንያና ሱዳን በሚገኙ ልዩ ልዩ የኦሮሞና የኤርትራ ገንዘብ የማስተላለፊያ መንገዶች (ዳሃብሽልና አማል ኩባንያዎች) አማካኝነት ገንዘብ እንዲላክለት ሁኔታዎችን አመቻችቶለት ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክና አማል ኤክስፐረስ የተሰጡ የገንዘብ ደረሰኞች (ሰነዶች) የገንዘበ ዝውውሩ መፈጸሙን አረጋግጠዋል።

በ2010 አጋማሽ ኡመር እድሪስ መሃመድ በጭፍራ አድርጎ ወደ አዲስ አበባ በየብስ በመጓዝ ለቡድኑ መተላለፊያ መንገድ እያፈላለገ አዳዲስ የጥቃት ዒላማዎችንም እያጠናና ቅኝት እያደረገ ወደ ኢትዮጵያ መዲና ስምሪት እንዲጀምር ጠዓመ ግዳጅ ሰጠው፡፡ የዚህ ግዳጅ ዒላማዎች የአፍሪካ ህብረት ዋና መሥሪያ ቤት፣ ቦሌ አየር መንገድ አካባቢ የሚገኘው ለንደን ካፌ፣ አክሱም ሆቴል፣ በሸራተን ሆቴልና በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት መካከል ያለው የፍል ውኃ አካባቢዎች ናቸው፡፡

ታዲያ ኡመር ተልዕኮውን በማጠናቀቅ ወደ ኤርትራ በመመለስ ኢን ከሚጠብቁት ሰልጣኞች ጋር ዳግም ተገናኘ፡፡ ኡመር እና "ድሮግባ" በታህሣሥ 2010 ከተመረቁ በኋላ፣ ከወዲ እያሱ ጋር አሰብ በመሄድ በፈንጅ ዙሪያ የማጠቃለያ ስልጠና ወሰዱ። ከጠዓመም ማብራሪያ ተሰጣቸው፡፡ ኡመር ከአጣሪ ቡድኑ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ የጠዓመን መግለጫ በራሱ አንደበት እንደሚከተለው ያስታውሰዋል፡፡

"ከተወጡኝ የጥቃት ዒላማዎች መካከል አንደኛው የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ነበር፡፡ ላንድ ክሩዘር ወይም የአፍሪካ ህብረት መሪዎችና መልዕክተኞች የሚይዙት ዓይነት ደረጃውን የጠበቀ መኪና እንድከራይ ተነገረኝ፡፡ ከ2 እስከ 4 የሚሆኑ ሲሊንደሮችን በማዘጋጀት በቢራ ሳጥን መሰል ነገር ውስጥ ከተሽከርካሪው የኋላ መቀመጫ ደብቄ እንዳስቀምጠው ተነገረኝ፡፡ ፊውዙን ደግሞ ከመኪናው ፊት ለፊት እንዳስቀምጠው ተደረገ። ከዚያም የአፍሪካ ህብረት ተሰብሳቢዎች ለሻይ የሚወጡበትን ሰዓት መውጫና

መግቢያቸውን ማጤን ነበረብኝ፡፡ ለጥቆም የሞባይሉን ማንቂያ ደወል በተመሳሳይ ሰዓት ሞላነው፡፡ በአቅራቢያው የሚገኝ ካፌ ወይም ሆቴል ተቀምጠን በመጠባበቅ መሪዎቹ በሚወጡበት ሰዓት ወደ ሞባይሉ እንድደውል ተደረገ፡፡

“ዓላማው መሪዎቹን ለመግደል አልነበረም፡፡ ይልቁንም አደጋ እንዳንዣበባቸውና ኢትዮጵያም እንደማትታደጋቸው ለማስጠንቀቅ ነበር፡፡ ይህን በማድረግም ኤርትራ የምትናገረው ትክክል መሆኑን ኢትዮጵያዊያን እንዲገነዘቡት ማድረግ ይቻላል፡፡ አንዳንድ የዓረብ ሀገራትም ደስተኞች ይሆናሉ፡፡

“ሌላኛው የጥቃት ዒላማ በሸራተን በቤተ መንግሥትና በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት አቅራቢያ የሚገኘው ፍል ውሃ ነው፡፡

“ሦስተኛው የጥቃት ስፍራ ደግሞ የአፍሪካ ትልቁ ክፍት ገበያ መርካቶ ነው፡፡ ይህም መንግስት ህዝቡን የመታደግ አቅም እንደሌለው ተገንዝቦ ህዝቡ ምሬቱን እንዲገልጽ ለመገፋፋት ነው፡፡ ፈንጅዎቹን ከሲሊንደሮች ጋር በመቀላቀል በአይሱዙ ፒክ አፕ መኪናዎች ላይ መጫን ነበረብኝ፡፡ ተሽከርካሪው እስከ 15 ሲሊንደሮችና ከ4 እስከ 6 ኪሎ ግራም የሚመዝኑ ሲ-4 ተቀጣጣይ ፈንጂዎች ይጫኑበታል፡፡ ሲሊንደሮቹም በፈንጅ አቀጣጣይ ተጠቅልለው አሊያም ተቋጥረው ከመኪናው ጋቢና ውስጥ ተበትነው ይቀመጣሉ። በውስጠኞቹ 6 ሲሊንደሮች ውስጥ ሲ-4 ከተቀበረ በኋላ ቀሪዎቹ 9 ሲሊንደሮች ደግሞ በፈንጅ አቀጣጣዩ ይጠቀለላሉ። ከዚያም ፊውዙ ከአደኛው ፈንጅ ማቀጣጠያ ጫፍ ላይ ተቋጥሮ በተንቀሳቃሽ ስልክ አማካኝነት እንዲፈነዳ ይዘጋጃል፡፡

“ጠዓመ ላፕቶፑን ከፍቶ የኢራቅ ሰርጎ ገቦች እንዴት አድርገው ከባድ ፈንጅዎችን እንደሚያቀነባብሩ ቪዲዮ አሳየኝ፡፡ ለማነሳሳት መሞከሩ ነበር። ከዚያም ላፕ ቶፑን በመዝጋት አዲስ አበባን ባግዳድ እናደርጋታለን አለኝ፡፡”

በተከታዩ ቀን ኡመር ከጠዓመና ገመቹ ጋር ዳግም በመገናኘት የመንግስት ደጋፊ ባንኮችን፣ የህዝብ ትራንስፖርት መገናኛ መረቦችንና የአዲስ አበባን ኃይል መቆጣጠሪያ ስለሚያጋዩበት ሁኔታ መከሩ፡፡ እንደ ኡመር አገላለጽ ከሆነ እሱና “ድሮግባ” 20 ኪሎ ግራም የሚገመቱ የሲ-4 ፈንጅዎችንና መቶ ሜትር የሚጠጋ RDX የፈንጅ ቆስቋሽ ገመድ (ዲቶኔተር) ከገመቹ ተቀብለዋል፡፡

ግዳጃቸውን ለመፈፀምም በመጀመሪያ በእግራቸው ወደ ጅቡቲ ተጓዙ፡፡ ከዚያም በተሽከርካሪ ድንበር አቋርጠው ወደ ኢትዮጵያ አቀኑ፡፡ በኢትዮጵያዊያን ፖሊሶችና የደህንነት ኃይሎች ላለመያዝ በእያንዳንዱ የጉዞ እንቅስቃሴ ወቅት የተወሰደ ጥንቃቄን ኡመር ለአጣሪ ቡድኑ ገልጿል፡፡ አዲስ አበባም እንደ ደረሱ ኡመር ፈንጅዎችንና ቁሳቁሶችን ለተልዕኮው እስከ ሚፈለጉበት ጊዜ ድረስ ሁነኛ ስፍራ እንዲያኖራቸው “ሙሳ” ለሚባል ሰው አስረከባቸው፡፡ ኡመር ከቡድኑ ጋር ቀድሞ አዲስ አበባ መጥቶ ትዕዛዝ በመጠባበቅ ላይ ከነበረው ፈቃዱ ጋርም ተገናኝቷል፡፡

አብዛኛዎቹ የመኪና አከራይ ኤጀንሲዎች ካለ አሽከርካሪ ስለማያከራዩና ለመግዛትም ቢሆን መታወቂያ ስለሚያስፈልግ ተሽከርካሪ ለማግኘት መቸገሩን ፈቃዱ ለኡመር አስረዳው። ከዚህ በተጨማሪም ኡመር ሰዎች በጋራ በሚኖሩበት ግቢ ውስጥ ቤት መከራየቱን ተመልክቶታል፡፡

አዲስ አበባ የደረሰው ቡድን ወይም ግብረ ሃይል ለዘመቻ እየተዘጋጀ ባለበት ወቅት፣ በኢን ያለው ቀሪ ሰልጣኝ ቡድን ደግሞ በየብስ አቋርጦ አዲስ አበባ ለመግባት በዝግጅት ላይ ነበር፡፡ “ኢማም” የተሰኘው የዚህ ቡድን አባል ለአጣሪ ቡድኑ እንደተናገረው፣ አንድ የኢን ሎጀስቲክ አቅርቦት መኮንን የጦር መሣሪያና ቁሳቁስ ለቡድኑ አሚልቶለታል፡፡ ግብረ ሃይሉ መንቀሳቀስ ሲጀምርም “ኢማም” ለዘመቻው የሚሆን የድራጉኖቭ ዓይነት ሰናይፐር ጠብ-መንጃ ተሰጠው፡፡ ቀሪዎቹ ደግሞ ክላሽንኮቭ ጠብ-መንጃና ጥይት ተከፋፈሉ፡፡ ኡመር ከጅቡቲ ካመጣቸው የመጀመሪያዎቹ ምልምሎች መካከል መሐመድ ኑር “ዶክተር” የቡድኑ መሪ ተደርጎ ተመረጠ፡፡

እንደ ኢማም እና ሰዒድ አብዱራህማን ኡሙር አገላለፅ ከሆነ፣ በመጀመሪያ ወደ አሰብ በመጓዝ የግዳጃቸውን ምዕራፍ የመጨረሻ መመሪያና ፈንጂዎችን ከገመቹ ተቀብለዋል፡፡ ግዳጃቸውም በየብስ ወደ ጭፍራ በማቅናት ፈንጅ መቅበርና ተጨማሪ ትዕዛዝ እስኪተላለፍላቸው መጠባበቅ ነበር፡፡…

…ይሁንና ይህ የተቀናበረው ዘመቻ የሰመረ አልነበረም። በጥር 2011 መግቢያ አካባቢ ዘመቻው ሲቃረብ ኡመር ተጨማሪ “ሥራ ማስኬጃ” ገንዘብ እንዲለቀቅለት ለገመቹ ጥያቄ አቀረበ፡፡ ሁኔታውንም በአንደበቱ እንዲህ ይገልፀዋል።…

…"ተጨማሪው ገንዘብ በአማል የሃዋላ አገልግሎት አማካኝነት ኡመር እንድሪስ በሚል ስም ከኬንያ ወደ አዲስ አበባ ተላለፈ፡፡ ከዚያም ተጨማሪውን 3 ሺህ ዶላር ለሶስቱ ሰዎች አከፋፍዬ ከአስመራ ይዘን ከመጣነውንና የተረፈውን አስልቼ ለራሴ አስቀረሁኝ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከሦስቱ ሰዎች ከአንዱ ጋር በተወዳጀናት እንስት አማካኝነት 500 ዶላር እንደሚልክልኝ ገመቹ ገለጸልኝ፡፡ እንስቲቷ እናኒ የምትባል የተስፋዬ (ፈቃዱ) ወዳጅ ስትሆን ወደ አስመራ የምትመለስ ነች፡፡ እርግጥም አጣሪ ቡድኑ እነዚህ ሁለት የገንዘብ ዝውውሮች ጥር 8 ቀን 2011 በኡመር የባንክ ሂሳብ ቁጥር መመዝገባቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ አግኝቷል፡፡

የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ሊጠናቀቅ በተቃረበበት በጥር የመጨረሻው ሳምንት ኡመር ከገመቹ ጋር መመካከር እንደሚገባው ተረዳ፡፡ ይህን ለማድረግ በሱዳን ሲም ካርድ ወደ ኤርትራ መደወል ወደ ሚቻልባት መተማ አቀና፡፡ ገመቹም አንዳንድ ጊዜ በተመሳሳይ ሁኔታ በሱዳንና ኢትዮጵያ ሲም ካርዶች መደወል ወደ ሚቻልበት ተሰነይ ይጓዝ ነበር፡፡ ታዲያ አጣሪ ቡድኑ ያገኛቸው የስልክ ጥሪ ሰነዶች እንደሚያስረዱት፤ ኡመር ኢትዮጵያ በነበረበት ወቅት ቢያንስ 39 ጊዜ ያህል ስልክ ተደዋውሏል፡፡

ብዙ ጊዜ ደዋዩ ገመቹ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ኡመር ከጠዓመና ዳውድ ኢብሳ ጋር አብረው በጠዓመ ቢሮ እንዳሉ በስልክ ተነጋግሯል፡፡ የጥሪ ሰነዶቹ እንደሚያሳዩት፤ ከጠዓመ ቢሮ ከተደረጉ ጥሪዎች አንዱ የስልክ ጥሪ የተደረገው በሱዳን እስር ቤት የሚገኝ የቀድሞ የኦነግ ካድሬ ከአጣሪ ቡድኑ ጋር በግንቦት 2011 ቃለ መጠይቅ ባደረገበት ወቅት ለቡድኑ በፈቃደኝነት ባስረከበው የስልክ ቁጥር ነው፡፡ አጣሪ ቡድኑ ኡመርና ጠዓመ በስልክ ሲወያዩ የሚያሰማ የተቀረጸ የድምጽ ሰነድ የደረሰው (በመንግስታቱ ድርጅት በድምጽ ላይብረሪ የተቀመጠ ነው) ሲሆን፤ የጣዕመ ድምፅ ትክክለኛነትም በገለልተኛ ወገን ተረጋግጧል።

ኡመር መተማ በነበረበት ወቅት በ"ዶክተር" የሚመራው ቡድን በኢትዮጵያ የደህንነት ኃይሎች ባቲ አቅራቢያ በቁጥጥር ስር መዋሉንና ከቡድኑ መካከልም ኢማም መቁሰሉንና መማረኩን በቴሌቪዥን መታየቱንም ተረዳ፡፡ ኢማም በቁጥጥር ሲውል በእጁ ይዞት የነበረው PSL (ድራግኖቭ) ሮማንያ ሰራሽ ስናይፐር ጠብ-መንጃ ከኢን ይዞት እንደመጣ ለአጣሪ ቡድኑ ተናግሯል፡፡ ሚያዚያ 11 ቀን 2011 የሮማንያ መንግስት በጻፈው ደብዳቤ መሣሪያውን በ2004 ለኤርትራ መከላከያ ሚኒስቴር እንደሸጠው በማረጋገጥ

ተጨማሪ ሰነዶችን አቅርቧል፡፡ መረጃው ለኤርትራ የመግሪያው ባለ ይዞታ መሆኗን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀትንም ይጨምራል።

ቀሪዎቹ የቡድኑ አባላት ተፍረክርከው ተበታትነዋል፡፡ ኡመር የአዲስ አበባ ተልዕኮውን አቋርጦ ቀሪ የቡድን አባላቱን ለመታደግ ወደ ባቲ ማቅናቱን ለአጣሪ ቡድኑ ተናግሯል፡፡ በህይወት ማግኘት የቻለው ግን ገርባ አካባቢ በጫካ ውስጥ ራሳቸውን የደበቁትን አሊን እና አብዲን ብቻ ነበር፡፡ ሁለቱም በፖሊስ ቁጥጥር ሲውሉ የቡድኑ መሪ “ዶክተር” ተገድሏል፡፡

ኡመርና በህይወት የተረፉት አዲስ አበባ ሲደርሱ የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ እንደቀጠለ ነው፡፡ ይሁንና የሚፈልጉትን ዓይነት ተሽከርካሪ ሳያገኙ ጊዜው ሊቀድማቸው ተቃርቧል፡፡ እናም የአፍሪካ ህብረት የጥቃት ዒላማ እንደማይሆን በመገመት ፊታቸውን ወደ ሁለት ታክሲዎች ላይ አነጣጠሩ፡፡ ስብሰባው የካቲት 2 ቀን 2011 ማለዳ ከተጠናቀቀ በኋላ አብዲና ፍቃዱ አክሱምና ሆቴል ፍል ውኃ አካባቢ ማነፍነፍ ጀመሩ፡፡ ከዚያም ኡመር ለሙሳ ደወለለትና ፈንጅዎችንና የፈንጅ ማቀጣጠያዎችን ስለሚረካከቡበት ሁኔታ ለመምከር ተስማሙ፡፡ ቁሳቁሶቹን ፒያሳ አካባቢ ከተረካከቡ በኋላ ኡመር ወደ ፈቃዱ ቤት አዛወራቸው፡፡

በቀጣዩ ቀን ማለዳ ፖሊስ ፈቃዱንና ተባባሪዎቹን ቤት ውስጥ እንዳሉ በቁጥጥር ስር አዋላቸው፡፡ ኡመር ወደ ፈቃዱ ለመደወል ሲሞክር የፈቃዱ ስልክ ዝግ መሆኑን ተረዳ፡፡ የሚያደርገው ግራ እየገባው የቡድኑን አባላት ወደ ሌላ አዲስ ሆቴል ወሰዳቸው፡፡ በተከታዩ ቀን ኡመር በህዝብ ማመላለሻ ሚዲባስ ላይ ተሳፈረ፡፡ ተሳፋሪው ሁሉ የሚያወራው ፖሊስ የፍንዳታ አደጋ ሊያደርሱ የተዘጋጁ ሰዎችን በቁጥጥር ስር ስለማዋሉ ነበር፡፡ እናም ኡመር ወደ ፈቃዱ ቤት መኳዙን ስርዞ ቀሪ የቡድኑ አባላት ወደ ኮምቦልቻ እንዲሸሹ አስጠነቀቃቸው፡፡ ወደ ፈቃዱ መኖሪያ ቤት ሲጓዝም ማንም አልነበረም፡፡ በእያንዳንዱ ዕለት ሆቴልና የሐሰት ሰነዶችን እያቀያየረ ጥቂት ከሰነባበተ በኋላ ወደ ናዝሬት አመራ፡፡ ግን በጉዞ ላይ ሳለ በቁጥጥር ስር ዋለ፡፡

ከአጣሪ ቡድኑ ጋር ቃለ ምልልስ ካደረጉ ተጠርጣሪዎች መካከል አስመራ ከሚገኙት የኦነግ አመራሮች በመደበኛነት የሚገናኘው የቡድኑ መሪ ኡመር እድሪስ መሃመድ

አማካኝነት ብቻ ነበር፡፡ ሌሎቹ የቡድኑ አባላት ከምልመላ ጊዜ ጀምሮ የስልጠና መመሪያ የሚቀበሉት ከኤርትራዊያን መኮንኖች ነው፡፡ ከኦነግ መዋቅር ፍጹም የተገለሉ ነበሩ፡፡

ኡሙር እንደሚለው እንደዚህ ዓይነት ዘመቻ መኖሩንና የዚህን ልዩ ዘመቻ ዓላማ የሚያውቀው የኦነግ ሊቀመንበሩ ዳውድ ኢብሳ ብቻ ነው— ዘመቻውን ለመምራትና ለመቆጣጠር ሲንቀሳቀስ ግን አይስተዋልም፡፡ እናም አጣሪ ቡድኑ እንደተገነዘበው፤ ዘመቻው በኦነግ ስም ቢራገብም የሴራው ዋነኛ ተዋናይ የኤርትራ ስለላ ተቋም ነው፡፡

የኤርትራን አስገራሚ ሁከት ፈጣሪነትን መንግስት አልባ ከነበረችው ሶማሊያ አኳያ ስንመለከት በተመሳሳይ ሁኔታ ታጣቂዎችን እየረዳች መሆኑን እንገነዘባለን። እንደሚታወቀው ኤርትራ የሶማሊያን ታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች መደገፍ የጀመረችው ከ1998 እስከ 2000 ድረስ በዘለቀው የድንበር ግጭት ምክንያት “አማራጭ ግንባር” ከፍታ ኦነግና ኦብነግ በመሳሰሉት የኢትዮጵያ ታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች አማካኝነት ኢትዮጵያን ለመምታት ትችል ዘንድ በሁሴን መሃመድ ፋራህ “አይዲድ” ከሚመራው አንጃ ጋር በተስማማችበት ወቅት ነው፡፡

በሶማሊያ ያላት ተሳትፎ ይበልጥ እያደገ የመጣው ደግሞ የእስላማዊው ህብረት ፍርድ ቤቶች በሰሜን ሶማሊያ እየገነነ በመጣበት ጊዜ እና የኢትዮጵያ ወታደራዊ ኃይል በታህሣሥ 2006 መገባደጃ በሶማሊያ ጉዳይ ጣልቃ መግባቱን ተከትሎ አል-ሸባብና የሶማሊያ ነጻነት ቡድኖች አስመራ ላይ ጥምረት በፈጠሩበት ወቅት ነበር፡፡

የኤርትራ መንግስት “በሶማሊያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት መርህ አለኝ” ይላል። ለሶማሊያ ታጣቂ ቡድኖች ወታደራዊ ድጋፍ እንደማያደርግ በተደጋጋሚ በማስተባበል ላይም ነው፡፡ ይሁንና አጣሪ ቡድኑ በሥራ ዘመኑ በቅርቡ ያገኛቸው ምንጮች እንደሚያረጋግጡት ኤርትራ ወታደራዊ ድጋፍ ስለማድረጓ የሚቀርቡባት ውንጀላዎች አብዛኛዎቹ እውነት ከመሆናቸውም በላይ፤ ከላይ በተጠቀሰው የውጭ ጉዳይ ዳይሬክተሯ አማካኝነት የሶማሊያ ታጣቂ ኃይሎችን በመርዳት ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ላይ ነች–እስካሁን ድረስ።...

...እንግዲህ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራትን ለማተራመስ ይህን ሁሉ ያልተሳካ ሴራን ሲፈፅም የነበረው የአስመራው አስተዳደር መሆኑን የፀጥታው ምክር ቤት ራሱ በመደበው ገለልተኛ አጣሪ ቡድን አማካኝነት አረጋግጧል። በዚህም ከአንዴም ሁለቴ የማዕቀብ ፅዋን

እንዲያነሳ አድርጎታል። አንዳንድ ሀገራትም ማዕቀቡን ተከትለው ውጭ ከሚኖሩ ዜጎቹ የሚሰበስበውን ቀረጥ እያስቀሩበት ነው። በዚህም ምክንያት መፈናፈኛ አጥቷል። እርሱም በተራው ሰላማዊ የማዕቀብ ፈንጂ ተጥሎበታል። እርግጥም "በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም" ይሏል ይህ ነው። አበቃሁ።